የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፯
አዲስ አበባ የካቲት ፳ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No.37
ADDIS ABABA 27th February, 2019

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፲፮/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በአልጀሪያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በእንስሳት እና ዓሳ እርባታ ዘርፍ የተደረገ ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ........ገጽ ፲፩ሺ፸፫

## Content

Proclamation No.1116/2019

Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the people's Democratic Republic of Algeria on the Field of Livestock and Fishery Proclamation --………………………..Page 11,073

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፲፮/፪ሺ፲፩

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአልጀሪያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስታት መካከል በእንስሳትና ዓሳ እርባታ ዘርፍ የተደረገውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአልጀሪያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በእንስሳትና ዓሳ እርባታ ዘርፍ የተደረገው ስምምነት ሚያዚያ ፭ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በአልጀርስ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### PROCLAMATION NO.1116/2019

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENTS OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE PEOPLE'S DEMOCRATIC REPUBLIC OF ALGERIA ON THE FIELD OF LIVESTOCK AND FISHERY.**

**WHEREAS,** the Agreement on the Field of Livestock and Fishery between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the People's Democratic Republic of Algeria has been signed in Algiers on the 13th day of April, 2017;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 6th day of February, 2019;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby Proclaimed as follows.

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በአልጀሪያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በእንስሳት እና ዓሳ እርባታ ዘርፍ የተደረገ ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፲፮ /፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ስምምነቱ ስለመፅደቁ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአልጀሪያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል ሚያዚያ ፭ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በአልጀርስ የተፈረመው ስምምነት ፀድቋል፡፡

**፫. አስፈፃሚ አካላት**

የግብርና ሚኒስቴር ይህን ስምምነት የማስፈፀም ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት ፳ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the people's Democratic Republic of Algeria on the Field of Livestock and Fishery Proclamation No. 1116/2019"

**2. Ratification of the Agreement**

The Agreement on the Field of Livestock and Fishery signed in Algeria on 13th April, 2017 between The Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the People's Democratic Republic of Algeria, is hereby ratified.

**3. Implementing Organ**

The Ministry of Agriculture is hereby empowered to implement this Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall come into force upon publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on this 27th day of February, 2019.**

**SAHLE-WORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**